# Seattle Kinijit Support Group and Development Association

## በሲያትል ቅንጅት ድጋፍ ሰጭ እና የልማት ማህበር

3815 S. Othello St. suite 100 #PMB137, Seattle WA 98118


# ኢንጂር ሀይሉ ሻውል በሲያትል ከተማ ደማቅ አቀባበል ተደረገላቸው!



በኢንጅነር ሀይሉ ሻውል የቅንጅት ለአንድነትና ለዲሞክራሲ ፓርቲ ሊቀመንበር የሚመራው የልዑካን ቡድን ዛሬ ጠዋት በሲያትል ከተማ አውሮፕላን ጣቢያ ሲደርሱ በከተማው የቅንጅት ደጋፊዎች ደማቅ አቀባበል ተደረገላቸው። ለቡድኑ ህጻናት ዕቅፍ አበባ ካበረከቱላቸው በኋላ በሥፍራው የተገኘው ሕዝብ በተለይም ሊቀመንበሩ ሙሉ ጤንነታቸውን አግኝተው በመሀከላችን በመገኘታቸው ደስታውን በእልልታ ገልጧል።

ልዑካኑ በሲያትል የሶስት ቀን ቆይታው፦

1. ባለፉት ሶስት አመታት የሲያትል ሕዝብ ላደረገው ድጋፍ ምሥጋናና አድናቆት ለማቅረብ
2. በወቅቱ የቅንጅትን ይዘት በተመለከተ ማብራሪያና ገለፃ ለማድረግ
3. የቅንጅት የወደፊት አላማና ጉዞን አስመልክቶ ማብራሪያና ገለፃ ለማድረግ
4. የቅንጅት ድጋፍ ሰጭ ድርጅቶችን አላማ ይዘትና ሚና ምን መሆን እንዳለበት መመሪያ ለመስጠት እንደሆነ ታውቋል።

በነገው እለት የሚደረገው አጠቃላይ የሕዝብ ስብሰባም በተለያዩ የሕዝብ መግናኛ አውታሮች በተለይም በኢትዮጵያ ዲያስፖራ ፓል ቶክ ለመላው አለም የሚተላለፍ መሆኑም ታውቋል። ቡድኑ በሲይትል የሚያከናውናቸውን ፕሮግራሞች በሙሉ እየተከታተልን እናቀርባለን።

*በሲያትል የቅንጅት ድጋፍ ሰጪ ማሕበር*

